የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN
COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የቴሌኮሚኒኬሽን ውድድር መመሪያ

# ቁጥር 798/2013

2013 ዓ.ም

## የቴሌኮሚኒኬሽን ወድድር መመሪያ

ጸረ ወደድር በሆኑ ባህሪያት ወይም ተግባራት ላይ ተሳትፈዋል ወይም ሊሳተፍ ይችላሉ የሚባሉ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮችን ማለየት የሚያስችል ሜቀፍ ማበጀት በማስፈለጉ፤

አግባብነት ያለው ገበያን መወሰን እና አግባብነት ባለው ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተርን ማስየም አስፈላጊ መሆኑን በማንዘብ፤

የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች በብቸኝነት እንዳይያዙ ማድረግ እና በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል ወድድር እንዲኖር ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን በሚዳት፤

የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወህደት ወይም የባለቤት ግዢን በተማለከተ ግምገማ ለማድረግ እና መወሰን የሚያስችል ሜቀፍን ማበጀት አስፈላጊ በመሆኑ ፤

በኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2019 አንቀጽ 6(2)፣ 47 እና 54(2) ማስረት ባለሥልጣኑ ይህንን የቴሌኮሚኒኬሽን ወድድር መመሪያ አወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የቴሌኮሚኒኬሽን ወድድር መመሪያ ቁጥር 798/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜዎች

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፤

1) "**ባለሥልጣን**" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1148/2019 መሠረት የተቋቋመ የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፡፡
2) "**የባለቤትነት ግዢ**" ማለት አንድ ኩባኒያ ሌላ ኩባኒያ መግዛቱን የሚያማለክት ሲሆን ግዢው የኩባኒያወን አክሲዮን ወይም ንብረት በመግዛት ሊፈጸም ይችላል።
3) "**ኮሎኬሽን**" ማለት አንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ለአገልግሎት አቅርቦት የሚጠቀምባቸውን የኔትዎርክ መሳሪያዎች ወይም ስርሃቶች የሌላኛው የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የኔትዎርክ መሳሪያዎች ወይም ሥርዓቶች የተገጠሙበት ስፍራ ላይ በሁለቱ መካከል በሚደረሰው ስምምነት መሠረት ቴክኒካዊ አግባብነት ባለው ቦታ በአንድ ላይ ማስቀመጥ ነው።
4) "**ድብልቅ ወህደት**" ማለት በተለያየ ሥራዎች ላይ በተሰማሩ ኩባኒያዎች መካከል የሚደረግ ወህደት ማለት ነው፡፡
5) "**ታችኛ ክዋኔ**" ማለት ተዋረዳዊ በሆነ ሚልኩ የተደራጀ እና በችርቻሮ ንግድ ላይ የተሰማራ ኦፕሬተር ሲሆን የችርቻሮ ንግድ አቅርቦቱን ሲያከናወን በህግ የተለየ እና ራሱን የቻለ ሌላ ተቋም ስራወን በሚስራበት ሚልክ ነው።
6) "**ታችኛ የችርቻሮ ወጪ**" ማለት የታችኛው ክዋኔ ወጪ ማለት ነው፡፡

7) “**አስፈላጊ ማልገያዎች**” ማለት በኢኮኖሚያዊ፣ ቴክኒካዊ ወይም በከበባዊ ሁኔታዎች ምክንያት ሊባዙ ወይም ሊተኩ የማይችሉ ቅጥር ግቢዎች፣ መሠረት ልማት ወይም የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ሀብቶች ማለት ነው፡

8) “**የጎንዮሽ ስምምነት**” ማለት በተመሣሣይ የገበያ ደረጃ በሚወዳደሩ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል በቃል ወይም በጽሑፍ በሚደረግ ተግባቦት የተቀናጀ አሰራርን ወይም የጋራ መግባባትን መፍጠር ነው።

9) “**የጎንዮሽ ውህደት**” ማለት በተመሣሣይ ገበያ የሚወዳደሩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ውህደት ነው፡፡

10) “**መሠረተ ልማት ማጋራት**” ማለት በተዋዋዮቹ መካከል የሚደረገው ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመሰረተ ልማት እና የኮሎኬሽን አቅራቢ ከመሰረተልማት እና ኮሎኬሽን ፈላጊ ጋር ቋሚ እና ገባሪ መሠረተ ልማቶችን የሚጋሩበት የተለያየ አሰራር ሲሆን የኔትወርክ ክፍሎችን፣ ሥርዓቶችን፣ መሣሪያዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ ቅጥር ግቢዎችን ወይም የመጠቀም መብቶችን ጨምሮ ሌሎችንም ያካትታል።

11) “**የህዳግ ጥበት**” ማለት አግባብነት ባለው የችርቻሮ ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ችርቻሮ ንግድ ወስጥ ላሉ ሌሎች ተወዳዳሪ የቴሌኮም ኦፕሬተሮች የጅምላ ሽያጭ በማከናወን የችርቻሮ ዋጋን እና የጅምላን ዋጋ ሲወስን እና ባስቀመጠው የጅምላ እና የችርቻሮ ዋጋ መካከል ያለው የዋጋ ልዩነት በችርቻሮ ንግድ ወስጥ ያለ የተሻለ አፈጻጸም ያለውን ተወዳዳሪ አገልግሎት እየሰጠ ወድድር ወስጥ መቆየት የማያስችለው ሁኔታ ሲከሰት የሚፈጠር ነው።

12) “**የገበያ ክለሳ**” ማለት ለቅድመ ወድድር ቁጥጥር ተጋላጭ የሆኑ የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎቶችን ማለየት እና መወሰን የሚያስችል በቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ወድድር ላይ የሚደረግ ክለሳ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ጉልህ የገበያ ድርሻ ያላቸው ተጽህኖ ፈጣሪ አካላትን መኖራቸውን እና ጸረ ወደድር የሆኑ ባህሪያትን ወይም ተግባራትን ለመግታት መወሰድ ስላላባቸው የመፍቴ እርምጃዎች ይወሰናል።

13) “**ውህደት**” ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የራሳቸው እልወና የነበራቸውየቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተሮች አንድ ወደ መሆን ማምጣት ወይም የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎቶች ለመስጠት ሀብቶቻቸውን በአንድነት በ—ማዋሃድ ነው፡፡

14) “**የውህደት እና የባለቤትነት ግዢ ማስወቂያ**” ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተርን የተመለከተ የውህደት ወይም የግዥ ስምምነት ወስጥ መግባት የፈለገ ሰው ለባለስልጣኑ የሚሰጠው ማስታወቂያ ነው።

15) “**ከገበያ ማስወጫ ዋጋ**” ማለት ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ተፎካካሪ ወይም ተፎካካሪ ሊሆን የሚቻልን የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ሆን ብሎ ለመጣል ወይም ማግል የሚችልበትን ሁኔታ በማሰብ ለአጭር ግዜ ኪሳር ወስጥ መግባት ወይም የሚያገኘውን ትርፍ መተው ነው።

16) “**ዋጋ**” ማለት አንድ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ለሚሰጠው የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት የሚያስቀምጠው ማናቸውም ክፍያ፣ ታሪፍ ወይም ሌላ አይነት ተከፋይ ገንዘብእና ተያያዥ የሆኑ የውል ይዘቶች እና ሁኔታዎች ነው፡፡

17) “**አግባብነት ያለው ገበያ**” ማለት አግባብነት ያለው የምርት ገበያን የሚያካትት ሲሆን በምርቶቹ ወይም አገልግሎቶች ባህሪያት፣ ዋጋ እና አጠቃም ምክንያት በተጠቃሚው ዘንድ ተተካኪ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ተደርገው የሚወሰዱ ሁሉንም ምርቶች ወይም አገልግሎቶችን የሚያጠቃልል እና/ወይም አግባብነት ያለው መልካ-

ምድራዊ ገበያ ሲሆን የሚግለከታቸው ኦፕሬተሮች ምርት እና አገልግሎታቸውን የሚቀርቡበት እና በበቂ ሁኔታ ተመሳሳይ የሆኑ የወደድር ሁኔታዎች ያለባቸውን አካባቢዎችን ያካታል፤

18) **"የችርቻሮ አገልግሎት"** ማለት ለሜጨሻ ተጠቃሚው ወይም ለደንበኛ የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን ለቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ አገልግሎትን አያካትትም፡፡

19) **"ጉልህ የገበያ ድርሻ"** ማለት ለኮሚኒኬሽን አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያዎችን ወይም በገበያ ወስጥ ያለውን ድርሻ አቅም በመጠቀም በኮሚኒኬሽን አገልግሎት ዋጋ ወይም አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚድረግ ችሎታ ነው፤

20) **"አነስተኛ ነገር ግን ተሻጋጋሪ ያልሆነ ጉልህ የዋጋ ጭማሪ መከራ"** ማለት የፍላጎት እና የአቅርቦት መተካካት ወጠቱን በመጠቀም አግባብነት ያለውን ገበያ ለመወሰን ተግባር ላይ የሚውል መንገድ ሲሆን ምናባዊ የሆነ አንድን ገበያ ለብቻው የተቆጣጠረ ኦፕሬተር በአንድ ሜልካ ምድራዊ አካባቢ እና ለተወሰነ ግዜ የሚቆይ ዋጋን ሲጨምር የሚፈጠር ነው።

21) **"ጉልህ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር"** ማለት አግባብነት ባለው ገበያ ወስጥ ጉልዕ የገበያ ድርሻ እንዳለው የተወሰነ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ሲሆን ለብቻው ወይም ከሌሎች አካላት ጋር በጥምረት በመሆን የሚፈጥረው ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም የገበያ የበላይነትን የሚሰጠው ሲሆን የኢኮኖሚው ጥንካሬ በሚሄይ ሜልኩ ከተወዳዳሪዎች፣ ደንበኞች እንዲሁም የሜጨሻ ተጠቃሚዎች ነጻ በሆነ ሜልኩ መንቀሳቀስ የሚያስችል አቅም ይሰጠዋል፡፡

22) **"ተተካኪ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች"** ማለት እርስ በእርስ በቀጥታ የሚወዳደሩ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ሲሆኑ በመካከላቸው ሊኖሩ የሚችሉ የፍላጎት ወይም የአቅርቦት ወገን መተካካት በዋጋቸው ላይ ጫና ይፈጥራል።

23) **በተዋረድ የተቀናጀ ኦፕሬተር"** ማለት የጅምላ እና የችርቻሮ አገልግሎት የሚሰጥ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ነው፡፡

24) **"ተዋረዳዊ ወህደት"** ማለት በተመሣሣይ የገበያ አቅርቦት ሰንሰለት ወስጥ በተለያየ ደረጃ የሚሰሩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች ወይም የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ወህደት ነው፡፡

25) **"የጅምላ አገልግሎት"** ማለት ለሌላ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ የቴሌኮሚኒኬሽን፣ የኮሎኬሽን ወይም የመሠረተ ልማት መጋራት አገልግሎት ነው፡፡

26) **"የስራ ቀናት"** ማለት ብቻ ሲሆን ቅዳሜ እሁድ እና ማኘቸውንም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ የበዓላት ቀን የተባለ ነው፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው –

1) አግባብነት ያላቸው ገበያዎችን ለመወሰን የሚያስችል ሜቀፍን ማዘጋጀት እንዲሁም አግባብነት ባለው ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተርን መወሰን፤
2) በአዋጁ አንቀጽ 48 ማስረት ጸረ ወደድር በሆነ ባህሪያት ወይም ተግባራት ላይ ተሳትፎል ወይም ሊሳተፍ ይችላል የሚባል የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተርን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ማየት የሚያስችል ሜቀፍን ማዘጋጀት፤

3) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች የገበያ ወደድርን በከፍተኛ ደረጃ በሚቀንስ ባህሪያት ወይም ተግባር ላይ እንዳይሳተፉ ሚድረግ፤

4) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወህደት ወይም የባለቤት ግዢን በተማከተ ግምገማ ለሚድረግ እና መወሰን የሚያስችል ሜቀፍን ማዘጋጀት ፤

5) የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች በብቸኝነት እንዳይያዙ ሚድረግ እና በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል ወድድር እንዲኖር ማረጋገጥ፡፡

6) የቴሌኮሚኒኬሽን ገበያወን ኢኮኖሚያዊ ወጤታማነት በጠቅላላው ማሻሻል፡፡

**4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ የማስረተልማት ማጋራት እና የኮሎኬሽን እንዲሁም የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት ሰጪዎችን ጨምሮ በሁሉም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወስጥ በሚገኙ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች እና የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ሰጪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ይሁን እንጂ በግልጽ ሲማለከት የተወሰኑ ድንጋጌዎች አግባብነት ባለው ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የባለሥልጣኑ ሚና</u>

**5. <u>የባለሥልጣኑ ሚና</u>**

1) ባለሥልጣኑ:

(ሀ) አግባብነት ያላቸወን ገበያዎች ለመወሰን፣ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያላቸወን ኦፕሬተሮች ለማለየት፣ ፀረ-ወድድር የሆነ አሰራርወይም ተግባር ላይ ተሰማርቷል ተብሎ የተወነጀለን ኦፕሬተር ለመሚርምር እና ወሳኔ ለማስጠት ፣ የተሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ላይ ተጽህኖ የሚፈጡ የወህደት ወይም የባለቤትነት ግዢ ሁኔታዎችን ለማገምገም እና ወሳኔ ማስጠት የሚያስችሉ እና ከፍተኛ መሎሚጫ የሚፈጥሩ ስታንዳርዶች እና የአሰራር ስርሃቶች የሚፍጠር ፤

(ለ) በየሦስት (3) አሞታቱ የገበያ ክለሳ የማከናወን፤

(ሐ) የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎትን የተማከተቱ ወድድሮችን ይቆጣጠራል፥ ከግዜ ወደ ግዜ አግባብነት ያላቸወን ገበያዎችን ይወስናል እንዲሁም በእነዚህ ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያላቸወን ኦፕሬተሮች የማለየም፤

(መ) በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ የወህደት እና የባለቤትነት ግዢ ማስወቂያዎችን ይገምግሚል እና ወሣኔ የማስጠት፤

(ሠ) በቴሌኮሚኒኬሽን አግለግሎቶች መካከል ወድድር እንዲኖር ወይም እንዲያድግ ከፍተኛ ጥረት የሚድረግ፤

ሃላፊነት አለበት።

2) ባለስልጣኑ:-

(ሀ) በራሱ ወሣኔ ወይም በሚማለከተው ወገን በሚቀርብ አቤቱታ መሠረት የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሩ በቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ገበያ ወስጥ በከፍተኛ ደረጃ ወድድርን የመቀነስ ዓላማ ወይም ወጤት ያለው ተግባር ወይም አሰራር ሚፈጸም አለሚፈጸሙ ለሚሚርምር ይችላል፤

(ለ) በኦፕሬተሮች መካከል ያለን ወድድር ጠበቆ ለማቆየት ወይም ኦፕሬተሮች በጸረ ወደድር ተግባራት ወይም ባህሪያት ላይ ተሳታፊ እንዳይሆን ለማድረግ በማሰብ፤ በገበያ ግምገማ የተገኙ ወጤቶች፥ በጸረ ወደድር አቤቱታዎች ላይ የተደረጉ ምርመራዎች እና አስፈላጊ ከሆነ የወህደት እና የባለቤትነት ግዢ ማስታወቂያዎች ላይ የሚደረግ ግምገማ ውጤትን መሰረት በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎች ወይም ቅጣዎችን ሊጥል ይችላል፤

## ክፍል ሦስት

## አግባብነት ያለውገበያ እና የገበያ ክለሳ

### 6. አግባብነት ያላቸውን ገበያዎች ስለመወሰን

1) ባለስልጣኑ ፡-

(ሀ) በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሚመለከተው ወገን በቀረበ አቤቱታ መሠረት ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገባቸው ገበያዎችን ለመለየት የሚያስችል የገበያ ግምገማ ለመጀምር ፤ በገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያላቸው ኦፕሬተሮችን ለመለየት እና ኦፕሬተሮች ላይ ግዴታ መጣል አስፈላጊ እንደሆነ ሲወስን ወይም

(ለ) በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሚመለከተው ወገን በቀረበ አቤቱታ መሠረት የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር በቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ገበያ ወስጥ ወድድርን በከፍተኛ ደረጃ የመቀነስ ዓላማ ወይም ወጤት ያለው ተግባር ወይም ሁኔታ ላይ መሳተፍ እና አለመሳተፉን ለመመርመር ሲወስን፤ ወይም

(ሐ) የወህደት እና የባለቤትነት የግዢ ማስወቂያን መሰረት በማድረግ የቀረበው የወህደት ወይም የባለቤትነት ግዢ የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ገበያን ወድድር በከፍተኛ ደረጃ የመቀነስ ወጤት አለው ወይም የለወም ብሎ ለመወሰን የቁጥጥር ሂደት መጀመር ያስፈልጋል ብሎ ከወሰነ፤

ለቴሌኮሚኬሽን አገልግሎቶች አግባብነት ያላቸውን ገበያን ሊወስን ይችላል።

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 1 ላይ በተዘረዘሩት ማናቸውም ሦስት ምክንያቶች የቁጥጥር ሂደት ለመጀመር ከወሰነ፤ ይህንን ተግባራዊ የሚያደርገው በአዋጁ አንቀጽ 34 እና ከ አንቀጽ 36 እስከ 38 በተዘረዘረው የአሰራር ስርሃት እና በዚህ መመሪያ መሠረት ነው፡፡

### 7. በገበያ ክለሳ ወስጥ የገበያ ወሰና

1) ባለሥልጣኑ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ ገበያዎችን ለመወሰን በየሦስት (3) አመቱ የገበያ ክለሳ ለማድረግ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል እንዲሁም በእነዚህ ገበያዎች ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያላቸው ኦፕሬተሮች ከተገኙ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያላቸው ኦፕሬተሮች በማለት ይሰይማቸዋል፤ ፡፡

2) የገበያ ክለሳው ዓላማ ሁሉንም የቴሌኮሚኬሽን ገበያዎች መለየት ላይ ያተኮረ አይደለም፡፡ ይልቁንም የገበያ ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል ተብሎ የሚታሰቡ ገበያዎችን ነው፡፡

3) አስቀድሞ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል ተብሎ የሚታሰብ ገበያን ለመለየት የሚከተሉት ሶስት መስፈርቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡ -

ሀ) ወደ ገበያ ለመግባት ወይም ለመስፋፋት ከፍተኛ እና ተሻጋሪ ያልሆኑ ገደቦች መኖራቸው፤

ለ) የገበያው አወቃቀር አግባብነት ባለው የግዜ ማጠን ወስጥ ወጤታማ የሆነ ወድድር እንዳይኖር ሜድረጉን እና

ሐ) የወድድር ህጎችን ተፈጻሚ ሜድረግ ብቻወን የገበያ መወደቅን በበቂ ሁኔታ መከላከል አለሜቻሉን፡፡

4) ባለስልጣኑ እነዚህን ገበያዎች ለይቶ ለሜከተል የወደፊት ምልከታ አካሄድ ይከተላል፡፡ ወደፊት ምልከታ አካሄድ ማለት የገበያወን ተለዋዋጭነት በማገናዘብ ከቅርብ ጊዜ እስከ መካከለኛ ጊዜ ሊኖር የሚችልን ወድድር ባህሪ ለመተንበይ ማጣርን ያካትታል፡፡

## 8. የፀረ- ወድድር ተግባር አቤቱታዎችን በተመለከተ የሜካሄድ ምርመራ አካል የሆነ የገበያ ወሰና

የፀረ-ወድድር ተግባራት አቤቱታዎች ላይ ምርመራ በሜካሄድበት ወቅት ባለስልጣኑ የሆላ ምልከታ አካሄድን ይከተላል፡፡ ይህ አካሄድ የሥነ ምግባር ጉድለት ተፈጽሟል ከተባለበት ጊዜ ጋር ተመጣጣኝነት ያለወን የጊዜ ርዝመት ወስዶ ይመረምራል፡፡

## 9. የወህደቶች እና የባለቤትነት የግዢ ማስወቂያ ክለሳ አካል የሆኑ ገበያዎች ወሰና

ባለሥልጣኑ ወህደቶችን እና የባለቤትነት ግዢ ማስወቂያዎችን በሚገመግምበት ጊዜ አግባብነት ያለው ገበያን የሂደቱ አካል በሜድረግ የገበያ ወሰና ወይም ልየታ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በዚህ ወቅት ባለሥልጣኑ የወደፊት ምልከታ አካሄድን የሚከተል ቢሆንም የቀረበው የወህደት ወይም የባለቤትነት የግዢ ጥያቄ በገበያው ላይ የፈጠረው መዋቅራዊ ለውጥ ወይምክምችት ከግምት ወስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## አግባብነት ያላቸወን ገበያዎች ለመወሰን የሜገለግል ጠቅላላ አቀራረብ

## 10. አግባብነት ያለው የምርት ገበያ

1) ባለሥልጣኑ አግባብነት ያለወን ገበያ በሜወስንበት ወቅት አገልግሎቱ የሚጥበትን ቴክኖሎጂ ከግምት ወስጥ ሳያስገባ በተቀራረበ ሜልኩ ሊተካኩ ይችላሉ የሚባሉ ሁሉንም አገልግሎቶች ማካተት ይኖርበታል፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች እርስ በርሳቸው በቀጥታ የሜወዳደሩ በመሆኑ በመካከላቸው የሜኖረው የአቅርቦት ወይም የፍላጎት መተካካት ዋጋቸው ላይ ተፅእኖ ይኖረዋል፡፡

2) አግባብነት ያላቸው ገበያዎችን ወሰን በሜስቀምጥ ጊዜ ባለስልጣኑ ገበያወን በብቸኝነት የተቆጣጠረ ምናባዊ አካል አለ የሜል የመላ ምት አካሄድን (ይህ አካሄድ በሌላ ስሙ በዋጋ ላይ አነስተኛ ነገር ግን ተሻጋሪ ያልሆነ ጉልህ ጭማሪ የሜያስከትል መላ ምት ይባላል) እና/ወይም ማናቸውም ሌሎች አግባብነት ያላቸወን የገበያ ትንተና ዘዴዎች ይጠቀማል፡፡

3) በቀላሉ ሊተካኩ በሚችሉ ምርቶችን መካከል የፍላጎት መተካካትን በተመለከተ ግምገማ በሜደረግበት ወቅት፤ ባለስልጣኑ ጉልህ ቁጥር ያላቸው የአንድ ምርት ተጠቃሚዎች ትንሽ ነገር ግን ተሻጋሪ ያልሆነ ጉልህ የዋጋ ጭማሪ ሲደረግባቸው ተተኪወን ምርት ወደ መግዛት ይሸጋገራሉ ወይ የሚለወን ግምገማ ማእከል በሜድረግ ነው።

4) በተጠቃሚው ዘንድ አገልግሎት "ሀ" እና አገልግሎት "ለ"በቀላሉ የሚተካኩ አገልግሎት ናቸው የሜል አመለካከት በሜኖርበት ወቅት በአቅርቦት ላይ ያለ የምርት መተካካት ሲገመገም፤ አንድ አቅራቢ አገልግሎት "ለ" ላይ ትንሽ ነገር ግን ተሻጋሪ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ ሲደረግ፤ አገልግሎት "ሀ' ማቅረብ በፍጥነት በመተው አገልግሎት 'ለ'ን ወደ ማቅረብ ይሸጋገራል የሚለወን ግምገማ ማእከል በሜድረግ ነው።

5) ባለስልጣኑ ትንሽ ነገር ግን ተሻጋሪ ያልሆነ ጉልህ የዋጋ ጭማሬ ሙከራ ሲያደርግ አስቀድሞ የፍላጎት ምትክ ግምገማ በማከናወን እጨ የገበያ ምርት በመድረግ በቡድን የተቀመጡ አገልግሎቶችን ይለያል። በመቀጠል ባለሥልጣኑ የአቅርቦት ምትክ በከል ያለውን ተፅዕኖዎች ከግምት ያስገባል፡፡

6) በፍላጎት በከል የሚኖር ምትክን በተመለከተ በቀረበ ማስረጃ ምክንያት አንድ አገልግሎት አግባብነት ባለው ምርት ገበያ ወስጥ ከተካተተ፤ ይህን አገልግሎት በተመለከተ የአቅርቦት ምትክ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም።

7) የፍላጎት ምትክ በሚገመገምበት ወቅት ባለስልጣኑ ከዚህ የሚከተሉትን ከግምት ወስጥ ያስገባል፡ -

   (ሀ) ደንበኛ ደንበኝነቱን በተመለከተ አገልግሎት ሰጪውን በቀላሉ የሚቀይርበት ሁኔታ፤

   (ለ) አገልግሎት ሰጪዊ መቀየር ያለው ጫና ወይም ወጪ

   (ሐ) አገልግሎቶቹ ከተጠቃሚው ልምድ አንጻር ያለው ወጠቅ እና ባህሪያት፤

   (መ) በነጠላ ከሚቀርቡ አገልግሎቶች ይልቅ በጥቅል ለሚቀርቡ አገልግሎቶች ገዢዎች ያላቸው ፍላጎት፤ እና

   (ሠ) በአገልግሎት ጥራት ላይ ግንዘቤ ሊወሰድበት የሚችል ልዩነትን ፤

8) በአቅርቦት በከል ያለው ምትክ በሚገምገበት ወቅት፤ ባለስልጣኑ ከዚህ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ወስጥ ያስገባል፡ -

   (ሀ) በስራ ላይ ያሉ አቅራቢዎች አንድን አገልግሎት ከማስጠት ወደ ሌላ ወደ ሌላ አገልግሎት ማስጠት በምን ያክል ፍጥነት ማሻጋገር ይችላሉ፤ ወይም

   (ለ) ለአዲስ አቅም ወይም አቅምን ለማስፋት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ኢንቨስትመንት ማድረግ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን እና ይህም ጊዜ የሚወስድ ተቋማዊ የወሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚጠይቅ መሆኑን፤ ወይም

   (ሐ) ያለን አቅም በፍጥነት በማስፋት አዲስ አገልግሎት ለመፍጠር ያለው የሕግ ወይም የቁጥጥር ገደቦች መኖራቸውን ፡፡

## 11. አግባብነት ያለው ሜላካዓ ምድራዊ ገበያ

1) ሜላካ-ምድራዊ ገበያዎችን በሚለይበት ወቅት ባለስልጣኑ በሜላካ ምድራዊ ስፍራዎች ወስጥ ያሉት የወድድር ሁኔታዎች በግልጽ በሚታይ ሜላኩ ምን ያህል እንደሚለያዩ መመርመር አለበት፡፡

2) የኔትወርክ ሽፋን ወይም ፈቃድ የተሰጠበት አካባቢ በባለስልጣኑ እንደ ጊዜያዊ አግባብነት ያለው ሜላካ ምድራዊ ገበያ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ሆኖም ግን የወድድር ሁኔታዎች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላው ከፍተኛ ልዩነት የሚያሳዩ ከሆነ ባለስልጣኑ ሌላ ሜላካ ምድራዊ ገበያ ሊወስድ ይችላል፡፡

# ክፍል አምስት

# የገበያ አቅም ስለ ማምገም

## 12. የገበያ አቅምን ማምገም

1) ባለስልጣኑ አንድ ኦፐሬተር ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው መሆኑወይም አለመሆኑን በሚለይበት ጊዜ ኦፕሬተር ለኮሚኬሽን አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ግባቶችን ወይም በገበያው ወስጥ ያለውን የገበያ ድርሻ አቅም በመጠቀም በኮሚኬሽን አገልግሎት ዋጋ ወይም አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ተጸዕኖ የመፍጠር ችሎታውን ይገመግማል፡፡

2) አንድ ኦፐሬተር ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው መሆኑ በሚጣጣምበት ወቅት ባለስልጣኑ በእነዚህ ሳይገደብ የሚከተሉትን ጠቋሚዎች ከግምት ውስጥ ያስገባል፤ እነዚህ ጠቋሚዎች በአንድነት ሲታዩ ጉልህ የገበያ ድርሻ መኖሩን ሊያሳዩ ይችላል፡-

(ሀ) የአገልግሎት ሰጪው የገበያ ድርሻ፡- የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ደንጋጌዎች በሌላ ሁኔታ እስካለስቀመጡ ድረስ፤ አንድ ኦፐሬተር አግባብነት ባለው ገበያ ውስጥ ከሃርባ ፐርሰንት (40%) በላይ የገበያ ድርሻ ሲኖረው፤

(ለ) አስፈላጊ ግብቶች ወይም ሀብቶች ላይ ያለው የቁጥጥር አቅም፤

(ሐ) የኢኮኖሚ ስኬል እና የኢኮኖሚ ስኮፕ፤

(መ) የተሻለ የቴክኖሎጂ አቅም ወይም የበላይነት፤

(ሠ) የተወዳዳሪ የመግዛት አቅም አለመኖር ወይም ዝቅተኛ መሆን፤

(ረ) ወደ ገበያው ለመግባት ወይም ለማስፋፋት ያሉ ተግዳሮቶች፤

(ሰ) ለፋይናንስ ያለ ተደራሽነት፤

(ሸ) የተለያዩ ምርት እና አገልግሎት ላይ ያለ ልምድ፤

(ቀ) በከፍተኛ ሁኔታ ያደገ የሽያጭ እና የስርጭት ጣጣር፤

(በ) ተዋረዳዊ ቅንጅት መኖር፤ እና፣

(ሸ) የሚቀመለስ ወጪ መኖር፡፡

3) በተናጥል ጉልህ የገበያ ድርሻ አላቸው ተብለው ያልተሰየሙ ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ኦፐሬተሮች እንደ አንድ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳላቸው ኦፐሬተሮ የሚንቀሳቀሱ ከሆነ፤ ባለስልጣኑ ኦፐሬተሮችን በጋራ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያላቸው ኦፐሬተሮች ብሎ ሊሰይም ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ጸረ ወድድር ተግባራት

### 13. ጸረ ወድድር ተግባራት

1) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፐሬተር በቴሌኮሚኒኬሽን ገበያ ውስጥ ወድድርን በከፍተኛ ሁኔታ የመቀነስ አላማ ወይም ውጤት ያለው ተግባር ላይ ጣሰማራት አይችልም፡፡

2) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፐሬተር ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር በቴሌኮሚኒኬሽን ገበያ ውስጥ ወድድርን በከፍተኛ ሁኔታ የመቀንስ ዓለማ ወይም ወጤት ያለው ስምምነት ወይም አሰራር ውስጥ መግባት አይችልም፡፡

3) ወድድርን በከፍተኛ ሁኔታ የመቀንስ ዓለማ ወይም ወጤት ያላቸው የሚከተሉት የጎንዮሽ ስምምነቶች ወይም የተቀናጁ ተግባርት የተከለከሉ ናቸው፦

ሀ) የአገልግሎት ወይም ከአገልግሎት ወጪ የሆኑ ዋጋዎችን የሚወስኑ፤ ወይም

ለ) ለአገልግሎት ዝቅተኛ የሆነ ዋጋ የሚያስቀምጡ፤ ወይም

ሐ) ጂኦግራፊያው ቦታዎችን፣ የተጠቃሚዎችን ዓይነት ወይም ወደ ገበያ ላለመግባት ስምምነት ሚድረግን ጣሰረት በሚድረግ የገበያን ድርሻ የሚያከፋፍሉ፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጸ 3 ላይ የጎንዮሽ ስምምነትን የተመለከተው ድንጋጌ ተግባራዊ የሚሆነው በተመሳሰይ የገበያ ደረጃ ለሚወዳደሩ የችርቻሮ ወይም የጅምላ ገበያ ወስጥ ላሉ ኦፕሬተሮች ሲሆን ድርጊቱ በጋራ መግባባት፥ በቃል ወይም በጽሁፍ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

5) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተደነገጉት ደንጋጌዎች ባለስልጣኑ አዋጁን ወይም በራሱ የጸደቁ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ ያስቀመጣቸው የአገልግሎት ዋጋ ወይም ደንብ እና ሁኔታዎችን ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

## 14) ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር ጸረ ወድድር ተግባራት

ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር ከአንቀጽ 15 እስከ 19 የተደነገጉ ተግባራት ላይ ማሳተፍ አይችልም፡፡ እነዚህን ተግባራት መፈጸም በገበያ ላይ ያለን የበላይነት አለአግባብ እንደማጠቀም ያስቆጥራል።

## 15. አገልግሎት አለማቅረብ ወይም ለማቅረብ ፍቃደኛ አለመሆን

1) ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር ለሌላ ኦፕሬተር ኢንተርኮኔክሽን፥ ኮሎኬሽን እና መሰረተልማት ማጋራት አገልግሎትን በባለሰልጣኑ የመሰረተ ልማት ማጋራት እና ኮሎኬሽን መመሪያ ላይ በተቀመጠው የግዜ ሰሌዳ ወስጥ እንዲሁም ምክንያተዊ በሆኑ ደንብ እና ሁኔታ እና ዋጋ ማቅረብ አለበት። ይህ አገልግሎት ማቅረብ ሊቀር የሚችለው በአዋጁ በመሰረተ ልማት ማጋራት እና የኮለሎኬሽን መመሪያ፥ በቴሌኮሚኬሽን ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ ወይም ሌላ በባለስልጣኑ በወጡ መመሪያዎች መሰረት ቴክኒካዊ በሆነ ምክንያት አገልግሎቱ ማስጠት ሳይቻል ሲቀር ብቻ ነው። ኦፕሬተር

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት አገልግሎቶችን አለማስጠት የሚከተሉትን እና ሌሎችንም ያካትታል:-

(ሀ) አስፈላጊ የሆኑ ግባቶችን ተደራሽ እንዳይሆኑ ማድረግ፤ ወይም

(ለ) ኢንተርኮኔክሽንን ማዘግየት ወይም ለኢንተርኮኔክሽን የሚደረግ ድርድር ረጅም ጊዜ እንዲወስድ ማድረግ፣ ሚጃ መከልከል፤ ወይም

(ሐ) የኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን ጥራትን መቀነስ ወይም የኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽንን መከልከል፡፡

3) የኢንተርኮኔክሽን፣ ኮሎኬሽን ወይም የመሠረተ ልማት ማጋራት የተሰጠው ምክንያታዊነት በጎደለው አኳኋን በመሆኑና ይህም ተወዳዳሪዎች ላይ ማዘግየት ከፈጠረ ወይም ተወዳደሪዎች ወደ አገልግሎት መግባት ወይም የሚስፋፉት ስራ መስራት አስቻጋሪ እንዲሆንባቸው ካደረገ፤ ባለስልጣኑ ይህንን ድርጊት አገልግሎቶች አለማቅረብ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ፍቃደኛ አንዳለመሆን ይቆጥረዋል፡፡

## 16. ተገቢ ያልሆነ መድልዎ

ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን፣ ኮሎኬሽን ወይም የመሠረተ ልማት ማጋራት አገልግሎቶች ታች ላለ ተወዳዳሪ አገልግሎት የሚያቀርብበት ደንብ እና ሁኔታዎች ለተመሳሳይ አገልግሎት ለራሱ ከሚሰጠው ደንብ እና ሁኔታዎች ያነሰ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ እና ይህም ከቴክኒክ፥ ከዋጋ ወይም ከሌላ አሳማኝ ምክንያት ጋር የተያያዘ ካልሆነ፤ ድርጊቱ ጸረ ወድድር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

## 17. ፀረ-ወድድር የሆኑ የጥቅል እና የማያያዝ ተግባራት

ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር በከፍተኛ ደረጃ ወድድርን የመቀነስ ዓለማ ወይም ውጤት ያለው ማናቸውም አገልግሎቶችን የማያያዝ ወይም ጥቅል የማድረግ ተግባራት ላይ መሳተፍ የለበትም፡፡ አገልግሎት የማያያዝ ወይም የጥቅል አሰራሮች ከዚህ የሚከተሉት እና ሌሎችም ወጤቶች ሊኖሩት ይችላል፡-

1) በገበያ "ሀ" ወስጥ ያለ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር "ሀ" የሚባል ምርቱን፣ በገበያ "ለ" ወስጥ ላለ ተወዳዳሪ ለሆነ ሌላ ኦፕሬተር ለማቅረብ "ለ" የሚፈልገወን ወይም የሚሻወን አገልግሎት እንዲገዛ የሚሌለግ፤
2) በገበያ "ሀ" ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር "ሀ" የሚባል ምርቱን በገበያ 'ለ' ወስጥ ላላ ተወዳዳሪ ለሆነ ኦፕሬተር ከወጪ አንጻር በማያዋጣ ዝቅተኛ ዋጋ ለማቅረብ ፤ ኦፕሬተር "ለ' የሚፈልገወን ሌላ ተጨማሪ አገልግሎት እንዲገዛ ማድረግ እና በዚህም የኦፕሬተር "ለ'ን ወጪ ከፍ የማድረግ ፍላጎት፤

## 18. ከገበያ ወጪ ማድረጊያ ዋጋ

ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር ሌሎችን ከገበያ ወጪ የማያደርግ ማንኛውም የዋጋ ትመና ላይ መሳተፍ የለበትም፡-

1) ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ተፎካካሪን ወይም ተፎካካሪ ሊሆን የሚችልን የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ሆነ ብሎ ለመጉዳት ወይም መጉዳት የሚቻልበትን ሁኔታ በማሰብ ለአጭር ግዜ ከሰር ወስጥ ከገባ ወይም የሚያገኘውን ትርፍን ከተው ፤ ተወዳዳሪወን ከገበያ ወጪ የማያደርግ ዋጋ ተጠቅሟል ይባላል፡፡
2) ባለስልጣኑ አንድ ዋጋ ከገበያ ለማስወጣት ሲባል የተወሰነ ነው ወይም ከገበያ ሊያስወጣ ይችላል የሚለወን ለማምገም ለአገልግሎቱ ወይም ለጥቅል አገልግሎት የወጣው ወጪ ለአገልግሎቱ ከተቀማጠው ዋጋ ያነሰ ነው የሚለወን ነጥብ ይመዝናል። ለአገልግሎቱ የወጣው ወጪ ከቀረበበት ዋጋ ጋር እኩል ወይም የበለጠ ከሆነ፤ ዋጋው ከገበያ ለማስወጣት የተቀማጠ ዋጋ ነው አይባልም። ባለስልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለወን ኦፕሬተር የበጀት አመቱን ወጪዎች ወይም ከተገኘ የቁጥጥር የሂሳብ ወጪዎችን እንደ ሚረጃ ምንጭ በመወሰድ የአንደን አገልግሎት ወጪዎችን ያሰላል።እነዚህ ሚረጃዎች የተገኙት ከቀደመው ዓመት ከሆነ ምክንያታዊ ማሻሻያዎች ይደረጋል።
3) ከገበያ ወጪ ለማድረግ ዋጋ ተሰጥቷል የሚሉ አቤቱታዎችን በሚዊምርበት ጊዜ ባለስልጣኑ ወጪውን ለመወሰን ከዚህ የሚከተሉትን የወጪ ሞዴል ዘደዎች ይጠቀማል፡ -
   (ሀ) በረጅም ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ ወይም
   (ለ) የተደመረ በረጅም ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ ፤ ይህም (የጋራ እና መደበኛ ወጪዎችን ያካትታል፡፡

## 19. የህዳግ ጥበት

1) ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር የሕዳግ ጥበት ተግባር ላይ ማካሔት አይችልም፦
2) ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር ጅምላ አገልግሎት የጠየቀን የአንድ ተወዳዳሪ የትርፍ ህዳግን ሆን ብሎ ለመቀነስ በማሰብ የጅምላ አገልግሎቱን ዋጋ ከፍ ካደረገ ወይም በሚወዳደርበት ገበያ ወስጥ

የችርቻሮ አገልግሎት ዋጋን ከቀነሰ ወይም ሁለቱንም ካደረገ በሕዳግ ጥበት ተግባር ወስጥ ተሳትፏል ይባላል፡፡

3) የሕዳግ ጥበት መኖሩን ወይም የሚከሰትበት እድል መኖሩን ለማግምም ባለስልጣኑ በችርቻሮ ዋጋ እና በችርቻሮ አገልግሎት ማጫዋጋ መካከል አዎንታዊ ህዳግ ያለ መሆኑን ይገመግማል፡፡

4) የችርቻሮ አገልግሎት ዋጋን ለማስላት ባለስልጣኑ በጅምላ ገበያ ወስጥ የሚፈለገወን ወይም አስፈላጊ የሆነወን ግብዓት ለማግዛት የወጣወን ወጪእንዲሁም ከታች ያለ የችርቻሮ ዋጋን ከግምት ያስገባል፡፡

5) የችርቻሮ አገልግሎት አቅርቦት ወጪ ለማስላት ባለስልጣኑ በተዋረድ የተቀናጀ ኦፕሬተር የታችኛው የችርቻሮ ወጪ እንደ የወጡታማ የችርቻሮ ተወዳዳሪ የታችኛው የችርቻሮ ወጪ በሚድረግ ተክቶ ሊወስድ ይችላል፡፡

6) ባለስልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለወን ኦፐሬተር የበጀት አመቱን ወጪዎች ወይም ማግኘት ከተቻለ የቁጥጥር የሂሳብ ወጪዎችን እንደ ሚጃ ምንጭ በመወሰድ በተወራድ የተደራጀ ጉልህ የገበያ ድርሻ ካለው ኦፐሬተር ጋር የተያያዘወን የታች የችርቻሮ ወጪዎችን ያሰላል። እነዚህ ሚጃዎች የተገኙት ከቀደመው ዓመት ከሆነ ምክንያታዊ ማሻሻያዎች ይደረጋል።ባለስልጣኑ ለችርቻሮ አገልግሎት የዋጋ መሠረትን ለመወሰን ከዚህ ከሚከተሉት የዋጋ ሞዴሎች ይጠቀማል:-

(ሀ) በረጅም ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ፤ ወይም

(ለ) የተደመረ በረጅም ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ዋጋ ፤ ይህም (የጋራ እና መደበኛ ወጪዎችን ያካትታል)፡፡

## 20. የፀረ-ወድድር ተግባራት ምርመራ እና የወሳኔ አሰጣጥ

1) ባለስልጣኑ ተጨባጭነት እና መሠረት ያላቸወን አቤቱታዎች ለማየት እና ሀብቶቹን በአግባቡ ለማሥራት እንዲያስችለው፤ አቤቱታአቅራቢው አቤቱት ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን የአዋጁን፣ የዚህን መመሪያ ወይም የወድድርን ሕግጋት አንቀጾች በግልጽ ማመልከት አለበት፡፡

2) አቤቱታ አቅራቢው የፀረ-ወድድር ተግባርን በተመለከተ የቀረበወን አቤቱታ ሊደግፉ ስለሚቹሉ አገልግሎቶቹ፣ ዋጋዎች፣ ወጪዎች፣ የአገልግሎት ደንብ እና ሁኔታዎች፣ የወሎች ወይም የክፍያ ማጠየቂያ ቅጂዎች እና ሌሎች ደጋፊ ሰነዶች ቀጥተኛ የሆኑ ሚጃዎችን ማካተት አለበት፡፡

3) ባለስልጣኑ በጽሑፍ የተዘጋጀ አቤቱታ በደረሰው በሃያ (20) የስራ ቀናት ወስጥ ለሁሉም ወገኖች የሚከተለወን ጠቅሶ ምላሽ ይሰጣል: -

(ሀ) ምርመራ ለመጀመር በቂ ማስረጃ አለመኖሩን ፤ ወይም

(ለ) ስህተት ፈጽሟል የተባለው ወገን ለቀረበበት አቤቱታ ምላሹን በአስር (10) የስራ ቀናት ወስጥ እንዲሰጥ ማሳወቁን፤ ወይም

(ሐ) በአዋጅ አንቀጽ 34 እና ከ36 እስከ 38 ባሉት አንቀጾች እንዲሁም በዚህ መመሪያ ማሰረት የተቀማጡየአሰራር ሰርሀቶችን ማበርት በሚድረገምርመራወን መጀመሩን፡፡

4) በአዋጁ አንቀጽ 52(3) መሠረት ባለስልጣኑ ሚቸወም የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር የሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ዳኝነት የማስጠት ስልጣን ያለው ሲሆን እንዲሁም ሚቸወም የአዋጁ፣ የዚህ መመሪያ ወይም

ባለስልጣኑ ባወጣቸው እና ተፈፃሚነት ያላቸው መመዘኛዎች መሠረት አግባብነት ያላቸውን መፍትሄዎች የመጠቆም ስልጣን አለው፡፡

5) ባለስልጣኑ መፍትሄዎች ወይም ቅጣቶች ለመጣል ከወሰነ፤ ውሳኔው ተመጣጣኝ፣ ከመድልዎ ነፃ እና ግልጽ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ውህደቶች እና የባለቤትነት ግዢ

### 21. የውህደት እና የባለቤት ግዢ ቁጥጥር

1) ፍቃድ የተሰጠው የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያተፍበት ውህደት ወይም የባለቤትነት ግዢ በባለስልጣኑ ፍቃድ ካልተሰጠው ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

2) የባለቤትነት ግዢ ወይም ውህደት ተፈጽሟል የሚባለው፡ -

(ሀ) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቀደም ብሎ ራሳቸውን ችለው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ፣ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች /ፍቃድ የተሰጣቸው/ ሲዋሃዱ ወይም የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ለማስጠት ሲባል ሀብቶቻቸውን በአንድነት ካሰሙ፤ ወይም

(ለ) አንድ ሰው ወይም የተሰባሰቡ ሰዎች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ፈቃድ ከተሰጠው የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ሰጪ አክሲዮኖችን ወይም ንብረቶችን ከገዛ፤ ወይም

(ሐ) አንድ ሰው ወይም የተሰበሰቡ ሰዎች በሌላ በማናቸውም መንገድ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ስራ አመራር ከተቆጣጠረ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ባለቤትነት ለመግዛት ወይም ለውህደት ስምምነት ለማድረግ ሃሣብ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው አስቀድሞ ባለስልጣኑ ለውህደቱ ወይም ለባለቤትነት ግዢው ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

4) ለቀረበው የውህደት ወይም የባለቤትነት ግዢ አካል የሆነው አንደኛው ወገን የታሰበው ውህደት ወይም የባለቤትነት ግዢ ይጠናቀቃል ተብሎ ከሚጠበቅበት ቀን ቢያንስ ከዘጠና (90) የስራ ቀናት አስቀድሞ ለባለስለጣኑ የውህደት ወይም የባለቤትነት ግዢ ማስወቂያ ማቅረብ አለበት፤ ከዚህም ጋር የሚከተሉት ሚጃዎች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡ -

(ሀ) የገዢዎችን፣ የሻጮችን፣ የእነርሱን ባለ አክሲዮኖች እና ተባባሪ ኩባንያዎችን ከ አምስት መቶኛ (5%) በላይ የባለቤትነት ድርሻ ፍላጎት ያለው ማንኛውም ሰው ጨምሮ በልውውጡ ውስጥ የሚሳተፉ የሁሉንም ሰዎች ማንነት፤

(ለ) የቀረበው ልውውጥ ሃሣብ መግለጫ እና የንግድ ሁኔታዎች ማጠቃለያ፤

(ሐ) በቀረበው ልውውጥ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸውን ሰዎች የፋይናንስ ሚጃ ጨምሮ የቅርብ ጊዜ አመታዊ የፋይናንስ መግለጫ

(መ) ስለተሰጡ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች፣ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ዋና ዋና መደቦች አመታዊ ገቢ እንዲሁም የቴሌኮሚኒኬሽን ወይም የመሠረተ ልማት መገልገያ አገልግሎቶች ለማስጠት ጥቅም ላይ የዋሉ ሀብቶች ዋጋዎች፤ እና

(ሠ) በጣም የቅርብ ጊዜ የሩብ አመት የፋይናንስ ሪፖርት፡፡

5) የመሀደት እና ግዢ ማስወቂያ በደረሰው በሰላሣ (30) የስራ ቀናት ጊዜ ወስጥ ባለስልጣኑ ማስወቂያ በማጠት ከዚህ ከሚከተሉት አንዱን ይፈጽሚል፡ -

(ሀ) ልወጠዥ ሚጽደቅ፤ ወይም

(ለ) ልወጡ ወድድርን በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል ብሎ ካሰበ የቀረበወን ሃሣብ ወድቅ ያደርጋል፣ ለዚህ ውሣኔ ማ ሻ የሆኑትን በዝርዝር ይገልፃል፤ ወይም

(ሐ) ጉዳዩን በይበልጥ በዝርዝር መመርመር የሚያስፈልገው ከሆነ የቁጥጥር ሂደት በማከፈት ወይም በሚጀመር ይህ ልወጥ የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎቶች ወድድርን በከፍተኛ ደረጃ የሚቀንስ ሚሆኑን ይፈትሻል፡፡

6) ባለስልጣኑ የወህደት ወይም የባለቤትነት ግዢ ግምገማ ለሚድረግ ከወሰነ ይህንን ተግባራዊ የሚያደርገው በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ 38 ባሉት ድንጋጌዎች እና በዚህ መመሪያ መሠረት ነው፡፡.

7) ባለስልጣኑ በቀረበው ልወጥ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ፈቃድ ለማስጠት ከወሰነ እና የልወጡ አካላት የሆኑት ወገኖች ልወጡ ከማጠናቀቁ በፊት ሊያሟቺው የሚገቡ መፍትሄዎች ወይም ግዴታዎች ካስቀመጠ እንዲህ ያሉት መፍትሄዎች ወይም ግዴታዎች በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ ወይም በማቸወም አግባብነት ባላቸው የወድድር ሕግጋት መሠረት ይሆናሉ፡፡

## 22. የወሀደት እና የባለቤትነት ግዢ ትንተና

1) ባለስልጣኑ የወህደት እና የባለቤትነት ግዢ ማስወቂያ ሲደርሰው ይህ ልወጥ በቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት ላይ ሊኖረው የሚቻለወን ወጤት በተማከከተ ምርመራ ያደርጋል፡፡

2) በወድድሩ ላይ የሚኖረወን ተፅእኖ በሚታነትንበት ጊዜ ባለስልጣኑ ልወጡ በፈቀድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ልወጡ በሌለበት ካሉት ሁኔታዎች ጋር በማነፃፀር ይሆናል፡፡

3) የቀረበለትን ልወጥ በሚታነትንበት ጊዜ ልወጡ ከዚህ በሚከተሉት ላይ የሚኖረወን ወጤት ከግምት ያስገባል፡ -

(ሀ) የምርት ዋጋዎች፤

(ለ) የአገልግሎት ጥራት፤

(ሐ) የምርት አይነት፤ ወይም

(መ) የምርት ፈጠራ፡፡

4) አንድ ልወጥ በተለይ ደግሞ በወህደት ጊዜ በወድድር ላይ ብዙወን ጊዜ አሉታዊ እና አዎንታዊ ወጤቶች ያስከትላሉ፡፡ ባለስልጣኑ እንዲህ ያለው ልወጥ በወድድር ላይ የሚኖረወን ግልጽ ወጤት መትንተን አለበት፡፡

## 23. የጎንዮሽ ወህደቶች አሳሳቢ የወድድር ጉዳዮች

የቀረበወን የጎንዮሽ ወህደት ሃሣብ በሚታነትንበት ወቅት ባለስልጣኑ ከዚህ የሚከተሉትን የወህደቱን አዎንታዊ እና አሉታዊ ወጤቶች ጨምሮ ሌሎችንም ከግምት ወስጥ ያስገባል: -

(ሀ) በገበያ ከምችት ላይ ሊከሰት የሚቻለወን ጭማሪ እና ይህም በዋጋዎች፣ በአገልግሎት ጥራት እና በምርት አይነቶች ላይ ሊኖረው የሚቻለው ተፅዕኖ፤

(ለ) በወሀደቱ ምክንያት የተዋሃደው አካል የኢኮኖሚ ማጠን ወይም ስፋት ሜጨሮ ምክንያት ሊኖረው የሚቻለው የአፈፃፀም ወጠቃሚነት እና ማጡን፤

(ሐ) የቀረበው ወሀደት ሊያስወግድ የሚቻለው ተወዳዳሪ አይነት፤ እና

(መ) የገበያ ባህሪያት ለምሣሌ ወደ ገበያ ለመግባት ወይም ለሚስፋፋት ያለ ቅለት፣ በአገልግሎት አቅርቦት ሜድረክ የሚኖሩ የቴክኒክ ለወጦች እና ከወሀደት በኋላ ባሉት አመታት በደንበኞች ምርጫዎች ላይ የሚኖሩ ለወጦች፡፡

## 24. የተዋረዳዊ ወሀደት አሳሳቢ የወድድር ጉዳዮች

የቀረበለትን ተዋረዳዊ ወሀደት በሚዝነትንበት ወቅት ባለስልጡ አጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር በፀረ ወድድር ሁኔታ ለማቀሳቀስ ያለወን ችሎታ ለማደብ የሚያስችሉየቁጥጥር ሥርሃቶች ስለመኖራቸው ከግምት ወስጥ ያስገባል፡፡ በተለይ በአዋጁ ወይም በሚኘቸወም በባለስልጡ ተፈፃሚ በተደረጉ መመሪያዎች ወስጥ ከኢንተርኮኔክሽን፣ ኮሎኬሽን፣ የመሠረተ ልማት ማጋራት እና ሕጋዊ ታሪፎች ጋር የተያያዙ ግዴታዎች ከግምት ይገባሉ፡፡

## 25. የድብልቅ ወሀደቶች አሳሳቢ የወድድር ጉዳዮች

ባለስልጡ በድብልቅ ወሀደት ምክንያት በስራ ወጠቃሚነት ላይ ማሻሻል ካለ ይህ በወድድር ላይ የሚያስከትለወን ተፅእኖ ከግምት ያስገባል፡፡

## ክፍል ስምንት

## መፍትሔዎች እና ቅጣቶች

## 26. መፍትሄዎች እና ቅጣቶች

1) በአዋጁ አንቀጽ 52(5) መሠረት ባለስልጡ ፍቃድ በተሰጣቸው የቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት አቅራቢዎች ላይ የሚወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች እና የሚጣሉ ቅጣቶች ተመጣጣኝ፣ ከመድልዎ ነፃ እና ግልጽ ነመሆን አለባቸው፡፡

2) በመመሪያው ከአንቀጽ ከ6 እስከ 12 የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሰረት በሜድረግ በተከናወነ የገበያ ግምገማ አማካኝነት አንድ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር አግባብነት ባለው ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው ከለየ ፤ባለስልጡ በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ ወይም በሚኘቸወም በባለስልጡ በወጣ መመሪያ መሠረት ግዴታዎች ይጥላል ወይም የመፍትሄ እርምጃ ያስቀምጣል፡፡

3) ባለስልጡ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተሩ በመመሪያው አንቀጽ 13 እና በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 20 ላይ በተቀመጠወ አሰራር መሠረት በፀረ-ወድድር ተግባር ላይ እንደተሳተፈ ካወቀ፤ ከዚህ የሚከተሉትን የመፍትሄ እርምጃዎች ወይም ቅጣቶች ሊጥል ይችላል: -

(ሀ) የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተሩ ወደፊት እንዲህ ካለው ተግባር እንዲቆጠበ ትዕዛዝ ማስጠት፤ ወይም

(ለ) ቅጣት መጣል ወይም ሁኔታወን ወደነበረበት መመለስ፤ ወይም

(ሐ) ፍቃድ ማገድ ወይም ማሰረዝ፡፡

4) ባለስልጡ በገበያው ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር በመመሪያው ከአንቀጽ 14እስከ 19 እና በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 20 ላይ በተመለከተው የአሰራር ስርሃት መሠረት በገበያው ያለወን

ተጽህኖአለአግባብ በማጠቀም ተግባር ላይ እንደተሰማሩ ባወቀ ጊዜ፤ ከዚህ የሚከተሉትን የመፍቴእርምጃዎችን ወይም ቅጣቶች ሊጥል ይችላል፡ –

(ሀ) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሩ ወደፊት እንዲህ ካለው ተግባር እንዲቆጠብ ትዕዛዝ ማስጠት፤ ወይም

(ለ) ቅጣት መጣል ወይም ሁኔታውን ወደነበረበት መመለስ፤ ወይም

(ሐ) ፍቃድ ማገድ ወይም ማሰረዝ፡፡

5) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 መሠረት በውህደት እና በባለቤትነት ግዢ ማስወቂያ ግምገማ ላይ የቀረበው ሃሣብ የልወወጡ አካል የሆኑ ወገኖች በቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ወድድር ላይ ሊኖረ የሚችለውን አሉታዊ ወጤት ለመቀነስ የተወሰኑ ግዴታዎችን ወይም መፍትሄዎችን ተፈፃሚ ቢያደርጉ ሊፀድቅ እንደሚችል ካወቀ፤ ባለስልጣኑ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡ –

(ሀ) በልወወጡ ተሳታፊ የሆነ አንድ ወገን በባለቤትነት የያዛቸውን ወይም የሚቆጣጠራቸውን ንብረቶች እና የባለቤትነት ጥቅሞች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በቀጥታ ከእርሱ ጋር ላልተሳሰረ ወገን ማሸጥ ወይም ማስተላለፍ፤ ወይም

(ለ) ከውህደቱ በኋላ ፈቃድ የተሰጠው የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ አግባብነት ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው እንደሆነ መቁጠር እና በባለስልጣኑ የሚቀመጡ አንዳንድ ግዴታዎችን ማክበር፤ ወይም

(ሐ) ሌሎች ባለስልጣኑ አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያስባቸውን ሁኔታዎች ፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ሕግ ስለማክበር እና ስለማስፈፀም

### 27. ሕግ ስለማክበር

ባለስልጣኑ ፍቃድ የተሰጠው አገልግሎት ሰጪ የዚህን መመሪያ እና የአዋጁን ድንጋጌዎች ማክበሩን ይቆጣጠራል፡፡

### 28. ሕግ ማስፈፀም

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ፣ አዋጁ እና ባለስልጣኑ ያጸደቃቸውን መመሪያዎች መሰረት በሚደረግ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሩ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሷል ብሎ ከወሰነ፤ በአዋጅ አንቀጽ 52 መሠረት እርምጃ የሚወስድ ሲሆን እርምጃው የገንዘብ ቅጣት ወይም ሁኔታዎችን ወደነበረበት መመለስ ሊሆን ይችላል፡፡

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 26 እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለስልጣኑ የሚያስቀምጣቸው መፍትሄዎች እና ቅጣቶች በአዋጁ አንቀጽ 52(6) መሠረት ፈቃድ ስለማሰረዝ፣ እገዳ እና ሌሎች የአስተዳደር እርምጃዎች እና ቅጣቶች እንዲሁም የቅጣት መጠኖች ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**29.ሚስጥራዊነት**

በዚህ መመሪያ መሠረት በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች የሚሰጥ መረጃ ሚስጥራዊ ከሆነ ባለስልጣኑ እንዲህ ያለውን መረጃ ሚስጥራዊነት ለማጠበቅ ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

**30. የይግባኝ መብት**

ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠው ማንኛውም ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በአዋጁ አንቀጾች 38 እና 39 መሠረት ሚሰሶ ሊታይ እና ይግባኝ ሊጠየቅበት ይችላል፡፡

**31. ሕግ ማስፈፀም**

የአዋጁን፣ የዚህን መመሪያ ወይም በባለስልጣኑ የወጣውን መመሪያ አለማክበር የአዋጁን አንቀጽ 52 ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ማድረግን ያስከትላል፡፡

**32. ማሻሻያ**

ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ለሁሉም ፈቃድ የተሰጣቸው አገልግሎት ሰጪዎች አስቀድሞ በማሳወቅ እና በአዋጁ መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር የመወያየት ሂደትን በመከተል ይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**33. ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን**

ይህ መመሪያ ከ______________ 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ _______ቀን ___________ 2013 ዓ.ም**

**ኢንጂነር ባልቻ ሬባ**

**የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ባለስልለጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**